 

# በኮቪድ-19 ወቅት የቤት እንስሳዎችዎን ደህንነት መጠበቅ

ኮቪድ-19ን በሚያመጣው ቫይረስ ውሻዎች እና ድመቶች ሊያዙ ይችላሉ።

ውሻዎች እና ድመቶች ኮቪድ-19ን ወደሰው ሊያስተላልፉ እንደሚችሉ የሚያሳይ ማስረጃ አሁን ላይ የለም።

የቤት እንስሳዎችዎን የራስዎትን ቤተሰብ እንደሚንከባከቡት ይንከባከቡ።

በክትባት አማካኝነት የኮቪድ-19 ስርጭትን መቀነስ እርስዎን እና የቤት እንስሳዎትንም ከበሽታዎ ይከላከላል፣ ስለዚህ እባክዎ ተራዎት ሲደርስ ይከተቡ።

Center for One Health Research
deohs.washington.edu/cohr

HEALTH SCIENCES LIBRARY
UNIVERSITY of WASHINGTON
University Libraries
hsl.uw.edu

# ኮቪድ-19 ካለብዎት ወይም ለኮቪድ-19 ከተጋለጡ

ሌላ የቤተሰብ አባል ለቤት እንስሳዎት እንክብካቤ እንዲሰጥ ያድርጉ።

ለቤት እንስሳዎት እርስዎ እንክብካቤ መስጠት ካለብዎት፣

- የቅርብ ንክኪን (እንደ ማሻሻት፣ መሳም፣ ከእነርሱ ጋር አብሮ መተኛት) ይተዉ።
- እነርሱ አካባቢ ማስክ ያድርጉ።
- ለእነርሱ እንክብካቤ ወይም የእነርሱን እቃዎች (ምግብ፣ መጠጦች፣ ማረፊያዎች፣ መጫወቻዎች፣ ወዘተ) ከመንካትዎ በፊት ወይም ከነኩ በኋላ እጅዎትን ይታጠቡ።

ድመቶች በቤት ውስጥ እንዲቆዩ እና፣ ከተቻለ ደግሞ፣ እንደልብ እንዳይንቀሳቀሱ ያድርጉ።

የቤት እንስሳዎት የታመመ ከመሰለ፣ የእንስሳት ሃኪም ጋር ይደውሉ።